# ትንሳኤ ፣ የትንሳኤ እንቅፋቶችና ቀጣይ የትግል አቅጣጫ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ለተሟላ የትንሳኤ ጉዞ ጀምራለች፡፡በተሳካ መንገድም ውጤት ማስመዝገብ ችላለች፡፡ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትንሳኤ ጉዞዋን ጊዝያዊ መንገራገጭ እያጋጠመው ነው፡፡ከዚህ ጊዝያዊ መንገራገጭ በማውጣት ወደ ተሟላ ትንስኤ ለመጓዝ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ዳግም በጥልቅ የመታደስ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡በተጨማሪም መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሁለተኛ ግዜ አውጀዋል፡፡

ኢትዮጵያን ከጊዝያዊ አለመረጋጋት በማውጣት ወደ ዘላቂ መረጋጋት ለማምጣት የኢትዮጵያ ህዝቦች/ዜጎች የነቃ ተሳትፎን ይጠይቃል፡፡በተጨማሪም ሙሁራን የመሪነት ሚናቸውን መጫወት ይገባቸዋል፡፡ይህ ፅሑፍም አሁን ተከስቶ ያለውን ግዝያዊ አለመረጋጋት በዘላቂነት ለመፍታት የሚየስችል ጠቃሚ አስተያየት የማበርከት ዓላማ ያለው ነው፡፡

ውድ አንባብያን ይህን አጭር ፅሑፍ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ፣ የትንሳኤ እንቅፋቶችና ቀጣይ የትግል አቅጣጫ በኢትዮጵያ በሚሉ ንኡሳን ርእሶች ተካፋፍሎ ቀርቧል፡፡በዚህ ፅሑፍ ካፒታሊዝም ለሚለው ቃል ርእሰማልነት በሚል ቃል መተካቴን ከወዲሁ ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡መልካም ንባብ፡፡

## 1.የኢትዮጵያ ትንሳኤ

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበራት ስልጣኔ በዘመነ መሳፍንት የኋልዮሽ መጓዝ መጀመሩን ብዙዎች ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ይህ ጉዞ ለማስቆም ብሎም ወደ ነበረችበት የስልጠኔ ማማ ለመመለስ ህዝቦች ባልተደራጀ መንገድ ታግለዋል ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡ጥገኛ ርእሰማልነት በመምራት የነበረ ዘውዳዊው ስርዓት የአፈና መዋቅሩን አጠናክሮ ቢቀጥልም የኢትዮጵያ ህዝቦች ለብሄራዊ ማንነታቸው መከበር ፣ ለፍትህ እኩልነት ፣ ለፍትሃዊ ሃብት ክፍፍልና የዝህቦች የስልጣን ባለቤትነት ሲሉ ትግላቸው አጥናክረው ቀጥለዋል፡፡በውጤቱም የ1966ዓ/ም ታላቁ ህዝባዊ አብዮት እንዲፈነዳ ምክንያት ሆኗል፡፡ህዝባዊ ዓመፁም የዘውዳዊው ስርዓት ስልጣን እንዲገረሰስ አደረገ፡፡ህዝባዊ ዓመፁን የሚመራ ብቁ መሪ ድርጅት ባለ መኖሩ ምክንያት ህዝብ ለስልጣን መብቃት አልቻለም፡፡በአንፃሩ በአጭር ጊዜ የተደራጀ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን ተቆጣጠረ፡፡የነበረው የመሳፍንት ስርዓት ማስቀጠል እንደማይችል የተገነዘበ ወታደራዊ መንግስት መሬት በማከፋፈል የህዝቡን ቁጣ ለማርገብ ተንቀሳቀሰ፡፡ጥገኛ ርእሰማልነት ለማስቀጠልም ሁሉንም መብቶች በአዋጅ አገደ፡፡

በሰላማዊና ዲሞክራስያዊ መንገድ ትግል መቀጠል እንደማይችል የተገነዘቡ የኢትዮጵያ ተራማጅ ሃይሎች የህዝቡን አብዮታዊ ጥያቄዎች በመያዝ፣በተደራጀ መንገድ ፕሮግራም በመቅረፅ መታገል ጀመሩ፡፡በወቅቱ ተደራጅተው ትግል ከጀመሩት ኢህአፓ ፣ መኢሶን ፣ ኦነግና ህወሓት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የህዝብ ጥያቄ በመያዝ ፕሮግራም በመቅረፅና በተደራጀ መንገድ ትግሉን ይጀምሩት እንጂ እነ ኢህአፓ ፣ መኢሶን ፣ ኦነግ በተሳሳተ የትግል አቅጣጫ ስለ ተጓዙ ለድል አልበቁም፡፡በአንፃሩ የኢትዮጵያ ትንሳኤ የሚያበስር የትግል ችቦ ለመጀመርያ ጊዜ በህዳሴው መስመርና በተደራጀ መንገድ ለካቲት 11/1967 ዓ/ም በትግራይ ደደቢት በረሃ በመለኮስ ምልአተ ህዝብ ከጎኑ በማሰለፍ

በተራዘመ የገጠር ትጥቅ ትግል ተጉዞ ለድል የበቃ ድርጅት በኢትዮጵያ **ኢህአዴግ** (ህወሓት ፣ ኢህዴን(ብኣዴን) ፣ ኦህዴድ ፣ ደኢህዴን) ብቻ ነው፡፡

ይህ የህዳሴ መስመር ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ተራማጅ ሃይሎች በየግዜው እንዲጎለብት በህዝብ ተቀባይነት አግኝቶ የመታገያ መስመር እንዲሆን ደክመዋል መስዋእትነትም ከፍሏል፡፡መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች በከፈሉት መስዋእትነት የጥገኛ ርእሰማልነት ስርዓት ጠበቃ የነበረውን ፋሽስታዊ ደርግ ግንቦት 20/1983ዓ/ም ተገረሰሰ፡፡በምትኩም ነፃ ሃገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ፣ ህዝቡ ከልማቱ በየደራጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ርእሰማልነት ስርዓት ለመገንባት ትግሉ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ጉዞ ታይቶ በማይታወቅ የዕድገት ደረጃ ለማስመዝገብ አስችሏል፡፡ ኢትዮጵያ ለመጀመርያ ግዜ ብዝሃነት የሚያስተናግድ ሕገ መንግስት አፅድቃ ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ህዝቦች ጥቅማቸው ለማስከበር የሚያስችል በነጻ ሓሳባቸውን የመግለፅ ፣ በነፃነት የሚደራጁበትና ሰላማዊ ትግል የሚካሄድበት መብትን ተጎናፅፈዋል፡፡

በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ የማይናቅ ዕድገት በኢትዮጵያ ትንሳኤ መመዝገብ ተችሏል፡፡ ግብርና መር ስትራተጂ ተግባራዊ መደረግ በመጀመሩ ምክንያት በተተገበረው መጠን አርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ ከዕድገቱ ተጠቃሚ ማደረግ ተችሏል፡፡ኑሮው ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ መሻሻልን ማሳየት ጀምሯል፡፡በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መንግስት በዘረጋው መሰረተ ልማት አርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ ተጠቃሚ መሆን ችሏል፡፡የትምህርትና የጤና ተጠቃሚ መሆንም ችለዋል፡፡በኢንዱስትሪ በኩል በተሰራው ስራም ከፍተኛ ዕድገት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡በንጉሱ ዘመን በፋብሪካ ተቀጥሮ ይሰራ የነበረው ሰርቶአደር 30000 የሚደርስ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በኢትዮጵያ ትንሳኤ ዘመን ሌላውን ትተን በማኒፋክቸሪንግ ዘርፍ ብቻ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ቁጥር 2.5 ሚልዮን መድረሱን ኢቢሲ በዜናው እወጃው አስነብቧል፡፡

በኢትዮጵያ ትንሳኤ ዘመን ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ወገኖች 23 % ፣ የአንድ ሰው አማካይ የዕድሜ ጣርያ 64 ዓመት መድረሱን የመንግስት ባለስልጣናት ገልፀዋል፡፡በኣጠቃላይ ኢትዮጵያ ለተከታታይ ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ኢኮኖሚያዊ እድገት ማስመዝገብ ችላለች፡፡በዲፕሎማሲም ተደማጭ መሆን የጀመረች ሃገር ሁናለች፡፡

ይህ እድገት ማስመዝብ የተቻለው የርእሰማልነት ስርዓት በትክለኛ መንገድ መገንባት በመጀመሩና ስርኣቱን በሞግዚትነት እየመራው ያለው ድርጅት ኢህአዴግ በብቃት እየመራ መምጣቱን ያሳያል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በቅርብ ግዜ እየታየ ያለው ግዝያዊ አለመረጋጋት በመገንባት ያለውን ርእሰማልነት መገንገራገጭ መጀመሩንና በሞግዚትነት እየመራ ያለው ኢህአዴግ በስርዓቱ ግንባታ ላይ ጉድለቶች እያሰየ መሆኑ መገላጫ ሁኖ መጥቷል፡፡

ከዓለም ዓቀፉ የርእሰማልነት ስርዓት ሂደት እንኳን ብንመለከት አሁን የደረሰበትን ከፍተኛ የእደገት ደረጃ መድረስ የቻለው በብዙ መንገራገጭና ካጋጠመው መንገራገጭ ለመውጣት ባደረገው ትግል መሆኑን በብዙ ምሁራን ይታመንበታል፡፡ካጋጣሙት መንገራገጭ ለመውጣት አንዳንድ ግዜ ደምአፋሳሽ በሆነ መንገድ ፈፅሞታል፡፡በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ከብዙዎቹ በጥቂቱ ለመግለፅ አንደኛና ሁለተኛ የዓለም ጦርነቶች እንዲሁም መይደይ(የሰራተኞች ቀን)ይጠቀሳሉ፡፡ከዚህ

በተጨማሪ ከውስጡ የወጡ ለስርዓቱ የወገኑ ምሁራን በየግዜው ከሚደርሰው መንገራገጭ ለመውጣት የሚያስችሉ ኢኮኖምያዊ ቀመሮች ትንታኔዎችና መፍትሄ በመስጠት እንዲሁም የስርዓቱ ሽግምንት ለተሰጡ መፍትሄዎች ተግባራዊ በማድረግ ከመንገራገጭ እየወጣ ወደ አዲስ ምዕራፍ እየተሸጋገረ እስከአሁኑ ድረስ መጥቷል፡፡ይህን የመሰለ የጥናትና ምርምር ሂደት የርእሰ-ዴሳውያን ሃይሎች/ኮሚኒስቶች/ ጥቃት ጭምር በመከላከል አሁን ለደረሰበት ደረጃ አድርሶታል፡፡አሁንም ቢሆን ስርዓቱ በመንገራገጭ ላይ ይገኛል፡፡ቀኝ አክራሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ተደማጭነት ማግኘት መጀመራቸውን ስርዓቱ መንገራገጭ መጀመሩን አመላካች ሁኖ ታይቷል፡፡ይህ ሂደት ዓለማችን ወዴት እንዲሚያመራት ከወዲሁ መተምበይ ከባድ አድርጎታል፡፡

በርእሰማልነት ግጭት የሚከሰትበት ዋና ምክንያት የጥቅም ቅራኔ የማይለየው ስርዓት በመሆኑ ነው፡፡በባለሃብቱና ሰራተኛው ፣ በበለፀጉና ባልበለፀጉ ሃገራት ፣ የበለፀጉ ሃገራት እርስ በርሳቸው፣ በስደተኛና በኣገሪቱ ዜጋ መኸከል ወዘተ የጥቅም ግጭት የሚንፀባርቅባቸው ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው ርእሰማልነት በመሰረታዊ ባህሪው ከዓለም ዓቀፋዊ ስርዓት ተመሳሳይ ባህሪ ያለው በመሆኑ ከጥቅም ቅራኔ/ከጥቅም ግጭት/ ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡ዓለም አቀፉ ርእሰማልነት በባለሃብቶቹ ፍላጎትና ይሁንታ የሚመራ ሲሆን በኢትዮጵያ በመገንባት የሚገኘው ርእሰማልነት ግን በሞግዚት ፖለቲካዊ አብዮታዊ ዲሞክራስያዊ ድርጅት የሚመራ መሆኑ የተለየ ባህሪ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡በሞግዚት ኣብዮታዊ ዲሞክራስያዊ ድርጅት የሚመራ በመሆኑ ብዙሃኑ በየደረጃው ተጠቃሚ የማድረግ ቅኝት የተላበሰ ባህሪ ያለው ስርዓት እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ያለው ስርዓት አጋጥሞት ካለው ችግር ለማውጣት መታየት ያለበት ከዓለም ዓቀፉ ባህሪውና ከራሱ የተለየ ባህርው በመነሳት መቃኘት ፣ መፍትሄ ማስቀመጥ ይጠይቃል፡፡ከዚህ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ርእሰማልነት ግንባታ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን የሚዳስስ የትንሳኤው እንቅፋቶች ወዲሚለው ንኡስ ርእስ እንሸጋገር፡፡

## 2. የትንሳኤው እንቅፋቶች

በኢትዮጵያ ትንሳኤ ወቅት እየተገነባ ያለው ስርዓት ርእሰማልነት መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህ ስርዓት የሚመራበት ፕሮግራም አብዮታዊ ድሞክራሲ ነው፡፡ይህ አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ ልማታዊ ዲሞክራሲ /የህዳሴ መስመር/ ብለን መጥራት እንችላለን፡፡አብዮታዊ ዲሞክራሲ ርእሰማልነትን ለመገንባት እንቅፋት የሚሆን ስርዓት በመጠራረግ በምትኩ ርእሰማልነት ለመገንባት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ፕሮግራም ነው፡፡ይህ በኢትዮጵያ በመገንባት ያለውን ርእሰማልነት በዓለም እንደታየው በባለ ቤቱ/ባለሃብት/ እየተመራ የሚገነባ ሳይሆን በሞግዚት ፓርቲ/ኣብዮታዊ ሙሁር እየተመራ የሚገነባ ስርዓት ነው፡፡ከዚህ የተለየ ባህሪው የተነሳ በተመረጠና በተቀናጀ የመንግስት ጣልቃ ገብነት የሚጠቀም የነፃ ገበያ ስርዓት ነው፡፡ይህ የተመረጠና የተቀናጀ ጣልቃ ገብነትም በብዙሃኑ ጥቅም ቅኝት የተቃኘ ስለሚሆን እቅዱ ሲታቀደም ሲተገበርም የህዝብ ተጣቃሚነት ማእከል ያደረገ እንዲሆን የግድ ይለዋል፡፡ህዝቡ በየደረጃው ተጣቃሚ በሚሆንበት ፈጣን እድገት ይመዘገባል የሚል ታሳቢ ያደርጋል፡፡በኢትዮጵያ በመገንባት ያለውን ርእሰማልነት የሰፊው ህዝብ የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቅ ስርዓት ነው፡፡

ይህ ስርዓት ነው በኢትዮጵያ ሁለገብ እድገት ማስመዝገብ ያስቻለው፡፡ውድ አንባብያን ከላይ የተጠቀሰውን እድገት ማስመዝገብ የቻለው ርእሰማልነት፣ አሁን ለምን መንገራገጭ ገጠመው የሚል

ጥያቄ ማንሳታቹህ አይቀሬ ነው፡፡የርእሰማልነት ስርዓት ከዓለማቀፋዊ ባህሪውና በሃገራችን ውስጥ እየተገነባ ካለው ርእሰማልነት የተለየ ባህሪ በመነሳት መመልከት ይገባል፡፡

ከዓለም ዓቀፋዊ የርእሰማልነት ስርዓት ባህሪ እንኳን ብንነሳ በጥቅም ቅራኔ የተሞላ ስርዓት በመሆኑ የኢትዮጵያ ርእሰማልነትም የሚጋራው ባህርያት አለው፡፡ከዓለም አንፃር የተገለፁት ቅራኔዎች በኢትዮጵያም የሚገለፅበት መልክ አለው፡፡ለምሳሌ የሰራተኛና አሰሪ ፣ ሃብት ያከማቹና ስራ ያጡ ወገኖች ፣ በገጠርና ከተማ ፣ በንፅፅር አደጉ የሚባሉ አከባቢዎችንና አላደግንም የሚሉ አከባቢዎች እንዲሁም ከበለፁጉ ሃገራት ያለውን ያልተመጣጠነ የትርፍ ክፍፍል ወዘተ የቅራኔው መገለጫ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ያለው ርእሰማልነት በሞግዚት እየተመራና እየተገነባ ያለ ስርዓት በመሆኑ ምክንያት ከዚህ ባህሪው የሚመነጭ ቅራኔም  መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡አንደኛው ቅራኔ ስርዓቱ ባለሃብቱ በሚፈልገው መንገድ እንዲገነባ ሲፈልግ መሪው ድርጅት/አብዮታዊ ሙሁሩ ደግሞ የብዙሃኑ ህዝብ ጥቅም እንዲረጋገጥ ስለሚፈልግ በዚህ ምክንያት የጥቅም አለመጣጣም ይፈጠራል፡፡ሁለተኛው ምክንያት በኢህአዴግ ውስጥ የተሰባሰበው ሓይል/አብዮታዊ ምሁር/ ከተዋላዋይ ባህሪው የሚመነጭ የህዝብ ትግል በሚቀዛቀዝበት ወቅት የራሱን ምኞት የሚፈልግበት ብሎም ወደ ገዢ መደብ ለመሸጋገር የሚዘጋጅበት እድል መኖሩና በሌላ በኩል በህዝቡ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲኖር የሚካሄደው ትግል ያዝ ለቀቅ የሚል በመሆኑ ተጨማሪ ምክንያት ነው፡፡

በህዳሴው መስመር አገላለፅ ለማስቀመጥ ያህል የልማትና ዲሞክራሲ ሃይሎች በአንድ በኩል ኪራይ ሰብሳቢዎች በሌላ በኩል ተሰልፈው የፈጠሩት ቅራኔ እየተካረረ መጥቶ አንዱን ከሌላው የበላይነት ማረጋገጥ ስለተሳነው የተፈጠረ አለመረጋጋት ነው በሚል መግለፅ ይቻላል፡፡በሌላ አገላለፅ ለመግለፅ ያህል መዋቅራዊ ለውጥ በኢትዮጵያ እንዲመጣ የሚሰሩ ሃይሎችና ይህ መዋቅራዊ ለውጥ እንዳይመጣ በሚፈልጉ ሃይሎች አንዱ በአንዱ ላይ የበላይነት መያዝ ባለመቻሉ የተፈጠረ ግዝያዊ አለመረጋጋት ነው ተብሎ ማጠቃለልም ይቻላል፡፡

ግዝያዊ አለመረጋጋት ሊፈጠር የቻለው እዛም እዚህም ያሉ ቅራኔዎች የበኩላቸውን ሚና ቢጫወቱም በዋናነት በሃብት ክፍፍል ላይ የታየውን የፍትህ መጓደል የፈጠረው መሆኑን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡መሪው ኢህአዴግ ይህንን ቅራኔ ለመፍታት ባሳየው ጉድለት መባባሱንም ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ይህንን  ችግር መኖሩን የተገነዘቡ መዋቅራዊ ለውጥ እንዳይመጣ የሚታገሉ የውስጥም የውጭም ሃይሎች ወጣቱ በተሳሳተ መንገድ እንዲነሳሳ በማድረግ ወዳ ያልተፈለገ ግጭት እንዲገባ መርተውታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱ ቅራኔዎች በንቃት በመከታተል መፍትሄ በማስቀመጥ ወደ ያልተፈለገ ግጭት እንዳያመሩ ማድረግ ካልተቻለ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዕንቅፋቶች መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡ ቅራኔዎች መፈታት ባለመቻላቸው የመጣ አለመረጋጋት እንዴት ነው በዛላቂነት መፈታት የሚቻለው የሚል ጠያቂ አይጠፋም፡፡መልሱ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ንኡስ ርእስ ስር ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ቀጥለን እንመልተከው፡፡

3. ቀጣይ የትግል አቅጣጫ በኢትዮጵያ

ኢህአዴግ ባካሄደው የህዳሴ እንቅስቃሴ ዓለም የመሰከረለት ዕድገት እንዲመጣ አስችሏል፡፡በየግዜው ለሚያጋጥሙት ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በማስቀመጥ ወደ ከፍተኛ ድል ለመድረስ የበቃ ድርጅት

ነው ኢህአዴግ፡፡ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ካሁን ቀደም ማለትም በ25 የሰላምና የልማት ዓመታት ባልታየ ሁኔታ በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥ ጊዝያዊ አለመረጋጋት ተከስቷል፡፡የተከሰተውን አለመረጋጋት በዘላቂነት ለመፍታት ኢህአዴግ በጥልቅ የመታደስ እንቅስቃሴ አካሄዳዋል፡፡ይህ የተካሄደው የጥልቅ ተሃድሶ እንቅስቃሴ የተፈለገውን ድል ማስመዝገብ ባለመቻሉ ኢህአዴግ ዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ከሌሎች ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ቀደም ብሎ ወደ ዳግም በጥልቅ የመታደስ እንቅስቃሴ ገብቷል፡፡የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ በህወሓት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ግምገማ ኣካሂዷል፡፡ከዛም በመቀጠል የህወሓት 7ኛው ድርጅታዊ ኮንፈረንስ ሁሉንም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋር ድርጅቶች ተወካዮች ጭምር በተገኙበት አካሄደዋል፡፡የህወሓት 7ኛ ድርጅታዊ ኮንፈረንስ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረትም የከፍተኛ ፣ መካከላኛና ጀማሪ ኣመራር የግምገማና ራስህን የማጥራት መድረክ ተካሂዷል፡፡ይህ ሂደት በአባልና በህዝብ መድረኮች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይተመንበታል፡፡ህወሓት አንዱን መድረክ ካካሄደ በኋላ የተገኙ ግብአቶችን በመጠቀም ፈጥኖ የማስተካከያ እርምት እየወሰደ በመሆኑ በህዝቡ ከፍተኛ አሜኔታና ለትግል የመነሳሳት መንፈስ ፈጥሯል፡፡ይህንን ሂደት አጠናክሮ እንደሚሄድበት በብዙዎች ዘንድ ይተመንበታል፡፡በሌሎች የኢህአዴግ ድርጅቶችም ጠበቅ ያለ ዳግም በጥልቀት የመታደስ ሂደት መጀመሩ ይታወቃል፡፡ይህ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ከዚህ በመቀጠል የሚቀርቡ ቀጣይ የትግል አቅጣጫዎች ዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ በሚያጠናክር መልኩ ቀርቧል፡፡

### 3.1.የኢህኣዴግ ዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት

በዚህ ዘመን ነፃ አገራዊ ኢኮኖሚ መገንባት የሚስያችል ርእሰማልነት ለመገንባት የተደራጀ አብዮታዊ ምሁር የሚመራው ጠንካራ ድርጅት ያስፈልጋል፡፡በኢትዮጵያ የኣብዮታዊ ምሁር መሪነት ያለው ጠንካራ ድርጅት፣ርእሰማልነትን መርቶ የመገንባት ብቃትና ችሎታ ያለው ድርጅት በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለው ኢህአዴግ ብቻ ነው፡፡ይህንን ድርጅት ለማጠናከር መስራት ታሪካዊ ግዴታን መወጣት ነው፡፡በዚህ አንፃር ኢህኣዴግ የጀመረው ዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡አባላቱና ህዝቡ በሚሰጡት አስተያየት በቅደም ተከተል እያስቀመጠ ወቅቱ የሚጠይቀው የማስተካከያ እርምት መውሰድ ኣለበት፡፡የአርሶ አደር/አርብቶ አደር፣ሰርቶ አደር፣አብዮታዊ ምሁር፣መላው የከተማ ነዋሪ በሙሉ ኢህአዲግ እያካሄደ ያለው ዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ የሚያግዙ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባችዋል፡፡

### 3.2.ለአባል ድርጅቶችና ለኢህኣዴግ ጉባኤ በብቃት መዘጋጀት

ለዳግም በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ወቅት እንደተገነዘብነው የአመራር ማስተካከያ መደረግ እንዳለበት ያመላክታል፡፡በህዳሴው እንቅስቃሴ የተጓደለውን አመራር በተለይ ማእከላዊ ኮሚቴ የሚያሟላው በድርጅታዊ ጉባኤ ነው፡፡ለዚህ ድርጅታዊ ጉባኤ ብቁ ዝግጅት ማድረግ ማለት ብቁ አመራር እንዲገኝ ማድረግ ማለት ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪም ለቀጣይ ሁለት ዓመት ድርጅቱ የሚመራበት እቅድ የሚፀድቅበትም ጭምር ነው፡፡ስለዚህ መድረኩ የፈጠራቸውን ብቁ አመራሮች ማዘጋጀት/ይህ ማለት በኔትዎርክ ሳይሆን በኣባላቱና በህዝቡ ንቁ ተሳትፎ መሆን ይገባል/ ፣ ሊስተካከሉ የሚገባቸው አሰራሮች የሚስተካከሉት በጉባኤ ስለሆነ በብቃት መዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡በሚስተካከሉ አሰራሮች ውስጥ ማእከላይ ኮሚቴ የሚሆን መመዘኛው ፖለቲካዊ

ውግንናው ፣ ፖለቲካዊና ሞያዊ ብቃት ፣ ሊኖረው የሚገባ የግል ሃብት ጣርያው ፣ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በመካከላቸው መኖር የሚገባው ዲሞክራስያዊ ግንኙነት ወዘተ ከግምት ውስጥ ማስገባት፡፡ጉባኤ የሚካሄደው በየሁለት ዓመቱ ቢሆንም ከዛበላይ አልፎ መጠባበቅያው ስድስት ወራቶችም እያለፉ ነው፡፡የድርጅቱ ህገ ደምብ በሚፈቅደው መሰረት ጉባኤው የተራዘመበት ምክንያት ለአባላቱ መግለፅና ፍቃድ መጠየቅ የሚያስፈልግ ከሆነ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡እንዲሁም የአባላት ይሁንታን ማግኘት ይገባል፡፡

3.3.ኢህአዴግ አዳዲስ የትግል አቅጣጨዎች ፣ አሰራሮችና እቅደችን ማዘገጀትና መተግበር አለበት

የዓለማችንም ሆነ የሃገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ከአሁን በፊት ወዳልነበረ አዲስ ምዕራፍ እያስገባን ነው፡፡ከሃገራችን ሁኔታና ከህዝባችን ዘለቂ ጥቅም በመነሳት ዓለማዊ ሁኔታውን በማገናዘብ ለዚህ የሚመጥን አዳዲስ አቅጣጫዎች ፣ አሰራሮችና እቅዶችን ማዘጋጀትና መተግበር ይጠይቃል/ለአብነት የባለሃብቱና ሰራተኛ ዓቅም መገንባትና አደራጃጀት ማጠናከር/፡፡ ኢህአዴግ በዚህ መንገድ ዝጉጁ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

3.4.በመገንባት ላይ ያለው ርእሰማልነት በጥናትና ምርምር መምራት

ከላይ እንደተመለከትነው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የበላይነቱን የተቆጣጠረው ርእሰማልነት ያደገው ለተገነባው ስርዓት በወገኑ ምሁራን ጥናትና ምርምር እንዲሁም ለሚቀርበው ጥናትና ምርምር መፍትሄ ተብለው ለሚቀርቡ ጉዳዮች የሚተገብር ጠንካራ ፓርቲና መንግስት በመኖሩ ምክንያት በአዎንታዊ ተመኩሮ መማር ያለብን ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ ልምድ በመውሰድ የራሳችንን ልምድ በመጨመርና በመቀመር በቀጣይነት የሚገነባው ርእሰማልነት ጥንካሬ ለማስቀጠል ፣ መፈታት ያለባቸው ቅራኔዎች መፍታትና ለመድረኩ የሚመጥኑ አቅጣጫዎች ለማስቀመጥ የሚያስችል የጥናትና ምርምር ተቋማትን ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ከሚደራጁት ተቋማት ምጡቅ አእምሮ ያላቸው ለህዝብ የወገኑ ምሁራን ተዋናይ የሚሆኑበት ዕድልም መፈጠር ይኖርበታል፡፡

ታጁ ሙሓመድያሲን

muhamedyassintaju@gmail.com

14/06/2010ዓ/ም